በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 1-0/80/07
Ref. No.
ቀን 26 ጥቅምት 2007
Date

**በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ**

**በያሉበት፣**

**ጉዳዩ:- የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ፣**

የገቢ ግብር ነፃ መብቶች አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 21/2001ን ለማሻሻል የወጣውን መመሪያ ቁጥር 102/2007 ተፈፃሚ እንድታደርጉ የመመሪያውን አንድ ገፅ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክንላችሁ መሆኑን እገልፃለሁ::

ከሠላምታ ጋር

በከር ሻሌ ዱሌ
ዋና ዳይሬክተር

**ግልባጭ:-**

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ሥራዎች ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር
- ለሀገር ውስጥ ታክስ ኘሮግራም ል/ድ/ሥ/ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር
- ለጉምሩክ ኘሮግራም ልማትና ድ/ሥ/ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር
- ለህግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ገ/ባለስልጣን፣</u>

ሰቢ

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

ስልክ ቁ / Tel. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ/ Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

# ገቢ ግብር ነጻ መብቶች አፈጻፀም መመሪያ ቁጥር 21/2001ን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 102/2007

የኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሰልጣን

አዲስ አበባ 2007 ዓ/ም

# ገቢ ግብር ነጻ መብቶች አፈጻፀም መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ
## ቁጥር 102/2007

ከግብር ነጻ የሚደረጉትን የወሎ አበል እና የመዘዋወሪያ አበል ክፍያዎች መጠን ከወቅቱ የአቅርቦቶች ዋጋ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን በማስፈለጉ የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 3 (ሰ)፣ (መ) እና (ሸ) እንዲሁም አንቀጽ 27 በተሠጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ማሻሻያ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ " የገቢ ግብር ነጻ መብቶች አፈጻም መመሪያ ቁጥር 21/2001ን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 102/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ማሻሻያ</u>

   መመሪያ ቁጥር 21/2001 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

   1. የመመሪያው አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 3 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተተክቷል፡፡

      3/ ለአንድ ወር የሚከፈል የመዘዋወሪያ አበል ከግብር ነጻ የሚደረገው ከጠቅላላ የወር ደሞዝ ከአንድ አራተኛ (1/4) የበለጠ አይሆንም፡፡ ይሁንና የሠራተኛው ጠቅላላ ደሞዝ አንድ አራተኛው ከብር 2200 የሚበልጥ ሲሆን ከግብር ነጻ የሚደረገው የመዘዋወሪያ አበል በማንኛውም ሁኔታ ከብር 2200 መብለጥ አይችልም፡፡

   2. የመመሪያው አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 4 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 ተተክቷል፡፡

      4/ አንድ ሠራተኛ የተቀጠረበትን ሥራ ለማከናወን ከመደበኛ የስራ ቦታው ውጪ ከ25 ኪ.ሜ በላይ ለሚያደርገው እንቅስቃሴ ከሚከፈለው የቀን የውሎ አበል ከግብር ነጻ የሚደረገው ከብር 225/ሁለት መቶ ሀያ አምስት/ ወይም ከደሞዙ 4% ከሁለቱ ከፍተኛ ከሆነው መጠን በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

      5/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 4 የተቀመጠው ቢኖርም የመንግስት ተቋማት ለተሸዋሚዎች እና ሠራተኞቻቸው ከመደበኛ የስራ ቦታ ውጪ ከ25 ኪ.ሜ በላይ ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚከፍሉት የቀን ውሎ አበል ግብር አይከፈልበትም፡፡

   3. የመመሪያው አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (5)፣(6) እና (7) በቅደም ተከተላቸው መሠረት ንዑስ አንቀጽ (6)፣ (7) እና (8) በመባል ተሻሽለዋል፡፡

3. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

   ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

በከር ሻሌ
የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር